# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
# በኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር
# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

ሐምሌ 1991
አዲስ አበባ

# ማውጫ

**<u>አርዕስት</u>** **ገጽ**


መግቢያ ........................................................................ 1

ጠቅላላ መመሪያ ........................................................................ 1

ክፍል 1 እና 2 (ቅጽ - 1) የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ መለያና
የተመረጠው ቤተሰብ አባላት የዲሞግራፊና የሥራ ሁኔታ ................. 3

ክፍል 1:- የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ መለያ ..................................... 3

ክፍል 2:- የተመረጠው ቤተሰብ አባላት የዲሞግራፊና የሥራ ሁኔታ ............. 4

ቅጽ 2ሀ እና 2ለ ........................................................................ 7

ቅጽ 3ሀ እና 3ለ ........................................................................ 9

ቅጽ 4 ........................................................................ 11

ቅጽ 5 ........................................................................ 11

## የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት የመጠይቅ እርማትና ኮድ አሰጣጥ መመሪያ

## (Editing and Coding Manual)

### መግቢያ

በገጠርና በከተማ የሚኖሩ ቤተሰቦችን የኑሮ ሁኔታ የሚመለከት ስታቲስቲካዊ መረጃ አስፈላጊነቱ እጅግ እያደገ በመምጣቱ በአሁኑ ወቅት በገጠርና በከተማ በናሙና በተመረጡ የቆጠራ ቦታዎች የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ ጥናቱ ግቡን እንዲመታ ከሚያደርጉት አስተዋጽኦዎች መካከል አንደኛው ከመስክ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በሚገባ እርሞና ኮድ ሰጥቶ ለሚቀጥለው የጥናቱ ክፍል የማስተላለፍ ሥራ ነው፡፡ ስለሆነም የኮድ አሰጣጥና እርማት የማድረግ ተግባር በጥንቃቄ መከናወን ይኖርበታል፡፡

### ጠቅላላ መመሪያ

1. የእርማቱና ኮድ አሰጣጡ ሥራ መከናወን ያለበት ለዚሁ በተዘጋጀው መመሪያ መሠረት መሆን እንዳለበት ማስታወስ ይገባል፡፡ አንዳንድ በዚህ መመሪያ ውስጥ ያልተጠቀሱ ነገሮች ሲያጋጥሙ ጥያቄዎቹን ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማቅረብ መፍትሔ እንዲሰጠው ማድረግ፡፡

2. ሥራውን ለማከናወን መነሻው በመስክ የተሞላው መረጃ ስለሆነ አስቀድሞ እያንዳንዱ መጠይቅ በትክክል ተሞልቶ መምጣቱንና የመጠይቁ ገጾች ሙሉ መሆናቸውን አረጋግጦ መረከብ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህም ሌላ አንዳንድ በመረጃው አሰባሰብ ጊዜ ያጋጠሙትን ሁኔታዎች የሚያብራሩና ከመጠይቁ ጋር ተያይዘው የመጡት አስተያየቶች በሚገባ መያዛቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡

3. እርማት በሚደረግበትና ኮድ በሚሰጥበት ጊዜ ሁሉ ሥራው ከሚመለከተው ኃላፊ/ተቆጣጣሪ ካልታዘዘ በስተቀር <u>ማንኛውም መረጃ ሰብሳቢው ያሰፈረው ነገር መፋቅ/መጥፋት የለበትም</u>፡፡ መረጃው እርማት የሚደረግበት ከሆነ ከሰፈረው መረጃ አጠገብ <u>መረጃው ከተጻፈበት ቀለም ልዩ በሆነ ቀለም እርማቱ ይደረጋል</u>፡፡

4. አንዳንድ አስተያየት የተሰጠባቸው መረጃዎች በእርማቱና በኮድ አሰጣጡ ወቅት ልዩ ትንቃቄ የሚሹ ስለሆነ ከማረም በፊት ተቆጣጣሪውን ማሳየት ያስፈልጋል፡፡ ከዚያም እርሱ በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ይሰራል፡፡

5. የእርማቱና ኮድ አሰጣጡ ሥራ ጽሕፈቱ በሚነበብና በንጽህና መሠራት አለበት፡፡

6. በእያንዳንዱ ዓምድ ኮድ ለማስፈር በተሰሩ ንዑስ ዓምዶች ሁሉ ኮድ የተሞላባቸው መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በተለይ መረጃው የሚቀነባበረው በኮምፒውተር

ስለሆነ መረጃውና የጥናቱ ትንተና ዘዴዎች የሚገናኙት በዚሁ በኮድ አማካይነት ብቻ ስለሆነ በከፍተኛ ጥንቃቄ መሠራት አለበት::

7. የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ መለያ ባልተሞላባቸው ቅጾች ሁሉ ቤተሰቡ በሚኖርበት አካባቢ ከሚኖሩ ለሌሎች ቤተሰቦች ከተሞላላቸው ቅጾች በማየት ይሞላል:: የቤተሰቡ አድራሻ መለያ በማናቸውም ቅጾች ካልተሞላ ሁኔታውን ለሚመለከተው ክፍል በማሳወቅ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ይሠራል:: ይህ አባባል ከሌሎች ቅጾች በማየት ወደ አልተሟላው ቅጽ ማሳለፍ የሚቻሉትን መረጃዎች ሁሉ ያጠቃልላል::

8. ዕቃዎችና አገለግሎቶች መታየት ከሚገባቸው ቅጾች ውጪ በሌሎች ቅጾች ሊገኙ ስለሚችሉ እነዚህን በሚመለከቱ ቅጾች ወስዶ ለማስፈር አስቀድሞ የእያንዳንዱን ቅጽ ይዘት ማወቅ ስለሚያስፈልግ ከቅጾቹ ጋር በደንብ መተዋወቅ አማራጭ የሌለው ግዴታ ነው::

9. በእያንዳንዱ ቅጽ ውስጥ መመዝገብ ያለበት ኮድ ከምን ጀምሮ እስከ ምን ድረስ እንደሆነ በየቅጾቹ ራስጌ የተገለፀ ስለሆነ ከዚያ ውጭ ያለ በታው በሌላ ቅጽ የተጻፈ ኮድ ካለ ሰርዞ ዕቃው/አገልግሎቱ መግባት ባለበት በትክክለኛው ቅጽ ውስጥ እስከ ተገቢው ኮድ መገልበጥ አለበት:: ዕቃው/አገልግሎቱ የገባው በተገቢው ቅጽ ከሆነና የተሰጠው ኮድ ግን ስህተት ከሆነ የሚስተካከለው ኮዱ ብቻ ነው:: ትክክለኛው የዕቃው/አገልግሎቱ ኮድ የሚገኘው «የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ የዕቃዎችና አገልግሎቶች ዝርዝር የመጠን መለኪያ» ተብሎ ከሚታወቀው የዕቃዎችና አገልግሎቶች ኮድ መጽሐፍ ነው::

10. ለአንድ ዓይነት ዕቃ ወይም አገልግሎት ዕቃው ወይም አገልግሎቱ የሚታወቅበት ከአንድ በላይ ኮድ አይኖረውም፣ ለአንድ ዓይነት ኮድ እንደዚሁ ከአንድ የበለጠ ዕቃ/አገልግሎት አይገኝለትም::

11. በአንድ ንዑስ ዓምድ ከአንድ ቁጥር በላይ መጻፍ ስለሌለበት ይህ በሚያጋጥምበት ሁሉ ተቆጣጣሪውን በማማከር ተገቢው እርማት ይደረጋል::

12. ከቅጽ 2ሀ እስከ ቅጽ 3ለ ድረስ ላሉ ቅጾች ሁሉ በዓምድ 13 የሚሞላው የወጪ/ገቢ ዝርዝር ኮድ እርማትና በነዚህ ቅጾች የሚሰፍረው የወጪ/ገቢ ዝርዝር (በዓምድ 12) እርማት በአንድ ጊዜ የሚከናወኑ ነገሮች ናቸው::

13. መጠይቆቹ በሚሞሉበት ወቅት የሜትሪክ መለኪያ ያልሆኑ የአካባቢ መለኪያዎች መታየት እንደሌለባቸው በመመሪያው ተገልጧል:: ሆኖም በአንዳንድ መጠይቆች እነዚህ የአካባቢ መለኪያዎች በስህተት ሊታዩ ስለሚችሉ ለተቆጣጣሪው በማሳየት መፍትሔ ማስገኘት ያስፈልጋል::

## ክፍል 1 እና 2 (ቅጽ - 1) የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ መለያና የተመረጠው ቤተሰብ አባላት ዝርዝር ሁኔታ:-

ይህ ቅጽ በሁለት ክፍሎችና በ24 ዓምዶች የተከፈለ ነው::

የመጀመሪያው ክፍል የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ መለያ ሲሆን ከንዑስ ዓምዶች 1 -20 የያዘ ነው:: ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የተመረጠው ቤተሰብ አባላት ዝርዝር ሁኔታ የሚመዘገብበት ሲሆን ከ21 - 37 ንዑስ ዓምዶችን ያጠቃልላል::

## ክፍል 1: የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ መለያ

ዓምድ 1 ወር:- ጥናቱ በሁለት ዙር የሚካሄድ ሲሆን በሰኔና ሐምሌ ወራት 1991 ዓ.ም. የሚጠናው የመጀመሪያ ዙር ሲሆን በዚሁ ዓምድ በንዑስ ዓምዶች 1 እና 2 ውስጥ መሞላት ያለበት ወሩ ሰኔ ከሆነ 1 በንዑስ ዓምድ 1 እና 0 በንዑስ ዓምድ 2 ወሩ ሐምሌ ከሆነ ደግሞ በንዑስ ዓምድ 1 እና 2 ውስጥ 1 ፣ 1 መሞላት አለበት:: በሁለተኛው ዙር ለሚካሄደው ደግሞ በታህሳስ ወር 1992 ለሚካሄደው «2» መሞላቱን መረጋገጥ አለበት:: በንዑስ ዓምድ 1 ውስጥ 0 ሲሞላ በንዑስ ዓምድ 2 ውስጥ ደግሞ 4 ይሞላል:: በጥር ወር 1992 ለሚካሄደውም በንዑስ ዓምድ 1 ውስጥ 0 ሲሞላ በንዑስ ዓምድ 2 ውስጥ 5 መሞላቱን መረጋገጥ አለበት::

ዓምድ 2 ክልል:- ጥናቱ የሚካሄድበት ክልል ስም በትክክል መሞላቱን መረጋገጥ እና ኮዱን በንዑስ ዓምዶች 3 እና 4 ውስጥ መሙላት ያስፈልጋል::

ዓምድ 3 ዞን:- ጥናቱ የሚካሄድበት ዞን ስም በትክክል መሞላቱን ማረጋገጥ እና ትክክለኛውን ኮድ በንዑስ ዓምዶች 5 እና 6 ውስጥ መሞላት አለበት::

ዓምድ 4 ወረዳ:- ጥናቱ የሚካሄድበት ወረዳ ስም ትክክለኛነት ተረጋግጦ ኮዱ በንዑስ ዓምዶች 7 እና 8 ውስጥ መሞላት አለበት::

ዓምድ 5 ከተማ:- ጥናቱ የሚካሄደው በከተማ ከሆነ የከተማው ስም በትክክል መሞላቱን ማረጋገጥና ኮዱን በንዑስ ዓምድ 9 ውስጥ መሙላት ያስፈልጋል:: ገጠር ከሆነ ደግሞ በንዑስ ዓምድ 9 ውስጥ ኮድ 8 መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ዓምድ 6 ከፍተኛ/ወረዳ:- ጥናቱ በከተማ የሚካሄድ ከሆነ የከፍተኛው ስምና ኮድ በትክክል መሞላቱን ማረጋገጠ ያስፈልጋል::

ማሳሰቢያ:- ጥናቱ በገጠር የሚካሄድ ከሆነ ንዑስ ዓምዶች ውስጥ ኮድ 88 መሞላታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ዓምድ 7 ቀበሌ ገበሬ ማኅበር:- በከተማ የቀበሌው ስም በገጠር ደግሞ የገበሬ ማኅበሩ ስም በዓምዱ በተሰጠው ቦታ መሞላቱን ማረጋገጠ ሲያስፈልግ ከንዑስ ዓምዶች 12-14 የቀበሌው ወይም የገበሬ ማኅበሩ ቁጥር በትክክል መሙላት ያስፈልጋል::

ዓምድ 8 የቆጠራ ቦታ ኮድ:- በመስክ ተሞልቶ መምጣቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ዓምድ 9 የተመረጠው ቤተሰብ የምርጫ ተራ ቁጥር:- ይህ ቁጥር በመረጃ ሰብሳቢው የሚሰጥ ሲሆን በገጠር መጠይቅ ከ1-16 በከተማ ደግሞ ከ1-20 ቁጥሮች ብቻ በንዑስ ዓምዶች 12-18 የተሰጠ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ከነዚህ ውጭ የተሞሉ ቁጥሮች ካጋጠሙ ተቆጣጣሪውን በማሳወቅ መፍትሄ ማግኘት ያስፈልጋል::

ዓምድ 10 የቤተሰብ አባላት ብዛት:- በንዑስ ዓምዶች 19 እና 20 የተሞላው ቁጥርና በክፍል 2 ዓምድ 12 ንዑስ ዓምዶች 21-22 የሚገኘው የቤተሰቡ አባላት የመጨረሻ ተራ ቁጥር ጋር እኩል መሆን አለበት:: ይህ ካልሆነ ግን ሁለቱ ቁጥሮች የሚታረቁበትን ዘዴ ከተቆጣጣሪው ጋር በመሆን መቃኘት ይገባል::

ዓምድ 11 የቤተሰብ ኃላፊ ሙሉ ስም:- በዚህ ዓምድ የቤተሰቡ ኃላፊ ሙሉ ስም የሚመዘገብበት ሲሆን በክፍል 2 ዓምድ 13 መጀመሪያ ላይ የተመዘገበው ስምና በዓምድ 14 ንዑስ ዓምድ 23 ኮድ 0 የተሰጠው መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

## ክፍል 2: የተመረጠው ቤተሰብ አባላት የዲሞግራፊና የሥራ ሁኔታ

ዓምድ 12 ተራ ቁጥር:- በዓምድ 13 የመጨረሻ የቤተሰብ አባል ሆኖ የተመዘገበው ሰው በዓምድ 12 የያዘው ተራ ቁጥር በክፍል 1 ዓምድ 10 ንዑስ ዓምዶች 19 እና 20 ከተመዘገበው ቁጥር ጋር እኩል መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ዓምድ 13 መደበኛ ቤተሰብ አባላት ሙሉ ስም:- የቤተሰቡ አባላት ስም የሰፈረበት ዓምድ ስለሆነ ምንም ዓይነት እርማት አይደረግበትም::

ዓምድ 14 ከቤተሰብ ኃላፊ ጋር ያለው ዝምድና:- በዚህ ዓምድ ሥር ባለው ንዑስ ዓምድ መረጃ ሰብሳቢው መሙላት ያለበት ቁጥሮች ከ0-8 ያሉ ብቻ ናቸው:: አባላቱ ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸውን ዝምድና የሚገለጹበት ኮዶች ሥር የሚገኙ ስለሆነ የተሰጠው መግለጫና ኮድ ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ዓምድ 15 ጾታ:- በዚህ ዓምድ በንዑስ ዓምድ 24 መታየት ያለባቸው 1 ወይም 2 ብቻ ናቸው:: መረጃ ሰብሳቢው በስህተት ኮድ ሳይሰጥ ቢቀር ተቆጣጣሪውን በማማከር የገለሰቡን ጾታ ከልዩ ልዩ ሁኔታዎች ጋር በማገናዘብ መሞላት ይኖርበታል::

ዓምድ 16 ዕድሜ:- ይህ ዓምድ መስክ ላይ ተሞልቶ የሚመጣ ነው:: ሆኖም በዚህ ዓምድ በንዑስ ዓምዶች 25-26 ከ97 በላይ ቁጥር መታየት የለበትም ከ97 በላይ የሆነ ቁጥር ከታየ 97 ተብሎ መስተካከል ይኖርበታል::

ዓምድ 17 ማንበብና መፃፍ ይችላሉ:- በዚህ ዓምድ በንዑስ ዓምድ 27 መታየት ያለባቸው ኮድ 1 ወይም 2 ብቻ ናቸው:: በዓምድ 17 በንዑስ ዓምድ 27 ኮድ 1 ለተሞላለት

ዓምድ 18 የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል :- በዚህ ዓምድ ሥር የቤተሰብ አባል በዓምድ 18 የፈጸማቸውን ከፍተኛ ክፍልና በንዑስ ዓምድ 28 የተሞላው ኮድ ተዛማጅ መሆን የኖርባቸዋል:: የማይጣጣሙ ሆነው ከተገኙ በዓምዱ ሥር በተሰጠው መግለጫ መሠረት የንዑስ ዓምድ 28 ኮድ መስተካከል አለበት:: 5 ዓመት ላልሞላቸው የቤተሰብ አባላት ዓምዱ ስለማይመለከታቸው መረጃ ተሞልቶ ከተገኘ መሠረዝ አለበት::

ዓምድ 19 የጋብቻ ሁኔታ:- ዕድሜው 10 ዓመትና በላይ ለሆነው እያንዳንዱ የቤተሰቡ አባል አስመልክቶ የሚሞሉት ኮዶች ከ1-5 ብቻ ናቸው:: በዚህ ዓምድ ሥር በሚገኘው ንዑስ ዓምድ 30 ላይ ዕድሜው 10 ዓመት ላልሞላው የቤተሰብ አባል መረጃ ተሞልቶ ቢገኝ መሠረዝ አለበት::

ዓምድ 20 ሥራ መሥራትና አለመሥራት:- ይህ ዓምድ ዕድሜው 10 ዓመትና በላይ ለሆነ የቤተሰብ አባል በሙሉ ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ሥራ መስራት ያለመስራታቸው ሲሆን ያለፉት 12 ወራትን አስመልክቶ ሁኔታ የሚጠየቅበት ነው:: በዚህ ዓምድ ንዑስ ዓምድ 31 መታየት ያለባቸው ቁጥሮች 1 እና 2 ብቻ ናቸው:: በዚህ ዓምድ የተሞላውን ኮድ በማየት የተቀሩትን ዓምዶች መቆጣጠር ያስፈልጋል:: ሀ/ በንዑስ ዓምድ 31 ላይ ኮድ 1 የተሞላላቸው ቤተሰቦች በንዑስ ዓምድ 32 ላይ ምንም ነገር ያልተሞላላቸው መሆናቸውና በንዑስ ዓምዶች 33-35 በንዑስ ዓምድ 33 ውስጥ ኮድ 5 ከተሞላ እስከ 36 ድረስ ግን በሙሉ የተሞላላቸው መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::
ለ/ በንዑስ ዓምድ 31 ላይ ኮድ 2 የተሞላላቸው የቤተሰብ አባላት በንዑስ ዓምድ 32 ላይ ኮድ እንደተሞላላቸው ማስተዋልና ሌሎቹ ዓምዶች ግን ማለትም /33-36/ ምንም ነገር አለመሞላቱን ማረጋገጥ ግዴታ ነው::

ዓምድ 21 በዓምድ 20 «የለም» ለመለሱ:- ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ የሆናቸው የቤተሰብ አባላት በዓምድ 20 በምርታማ ተግባር መሰራታቸውን ተጠይቀው በንዑስ ዓምድ 31 ኮድ «2» ለተሞላላቸው በዓምድ 21 ላይ «ያልሰሩበት ምክንያት» የሚጠየቅላቸው ሲሆን መሞላት ያለባቸው መልሶችና ኮዶችም በዓምዱ ሥር ከተዘረዘሩት ውስጥ ነው:: ስለዚህ በዓምዱ የተሞላው መልስና ለመልሱ የተሰጠው ኮድ መጣጣማቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: የማይጣጣሙ ከሆኑ ተቆጣጣሪውን በማማከር እንዲስተካከል ማድረግ ያስፈልጋል:: ከዚህም ሌላ:-

ሀ. ዕድሜያቸው የማይፈቅድላቸው የቤተሰብ አባላት (ማለትም ከ10 ዓመት በታች) መረጃ ከተሞላላቸው መሠረዝ ያስፈልጋል::

ለ. በዓምድ 20 ንዑስ ዓምድ 31 ላይ ሰርተናል ብለው ኮድ «1» የተሞላላቸው የቤተሰብ አባላት ዓምድ 21 ከተሞላላቸው መሠረዝ ያስፈልጋል::

ዓምድ 22-24 እነዚህ ዓምዶች የሚሞሉት በዓምድ 20 ንዑስ ዓምድ 34 ላይ ኮድ «1» የተሞላላቸው ከሆነ ብቻ ነው።

ዓምድ 22 የቅጥር ሁኔታ፡- በዓምድ 22 በተሰጠው ክፍት ቦታ የተሞላውን የቅጥር ሁኔታ በንዑስ ዓምድ 33 ከተሞላው ኮድ ጋር መጣጣሙን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

ዓምድ 23 የሥራ ዓይነት፡- በዓምድ 20 ላይ ሰርቻለሁ በማለቱ ንዑስ ዓምድ 31 ውስጥ ኮድ 1 የተሞላለት የቤተሰብ አባል በዓምድ 22 ሥር በሚገኙ ክፍት ቦታዎች ላይ ዋነኛ ሥራው ምን እንደ ነበር ተጠይቆ ተሞልቷል። ስለሆነም ለዚህ የሥራ ዓይነት የተሰጠው የመለያ ኮድ ከ«የሥራ ዓይነትና የድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት ምደባና መለያ ኮድ ዝርዝር» በመውሰድ ኮዱ በንዑስ ዓምድ 34 እና 35 ውስጥ የሞላል።

ዓምድ 24 የመንግስት ተቀጣሪ ከነበሩ የት ነበር የሚሰሩት፡- በዓምድ 22 ተቀጣሪ የመንግስት ተብሎ በንዑስ ዓምድ 33 ውስጥ ኮድ 5 ለተሞላላቸው የቤተሰብ አባላት በዓምድ 24 ሥር በሚገኙ ክፍት ቦታዎች ላይ የሚሰሩበት መ/ቤት እና በንዑስ ዓምድ 36 እና 37 ውስጥ የተሞላው ኮድ የሚጣጣም መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

## ቅጽ 2ሀ እና 2ለ

## በሳምንቱ ውስጥ ለቤተሰቡ ፍጆታ የዋለ የምግብ፣ የመጠጥና የትንባሆ ጠቅላላ መጠንና ዋጋ/በግዥ፣ በነፃ፣ ከቤተሰብ ድርጅት ...ወዘተ. የተገኘውን ያጠቃልላል:: /ከኮድ 00001 - ኮድ 02098

እነዚህ ቅጾች የምግብ፣ የመጠጥና የትንባሆ ፍጆታን ያጠቃለለ ሲሆን ከ00001-02098 ያሉ ኮዶች ብቻ ተመዝግበውበታል:: ከነዚህ ኮዶች ውጭ የተመዘገበ ኮድ ከተገኘ የዕቃውን ስም በማየትና የኮድ መጽሐፍ በመጠቀም ትክክለኛ ኮድ ይሰጠዋል:: የኮዶች ዝርዝር በኮድ መጽሐፍ ከገጽ 1 - ገጽ 10 ባሉት ገጾች ሰፍሮ ይገኛል:: በቅጾቹ ጫፍ ላይ በተሰጡት ክፍት ቦታዎች የጥናቱ ወር 9 የአካባቢ መለያዎች መመዝገባቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ያልተመዘገበ መረጃ ከተገኘ ከሌሎች ገጾች በመውሰድ ይሞላል::

ዓምድ 12 ለፍጆታ የዋለ የምግብ፣ የመጠጥና የትንባሆ ዝርዝር:- በዚህ ዓምድ መመዝገብ ያልነበረበት ዕቃ ከተገኘ በመሰረዝ በትክክለኛ ቦታው ማለትም ወደ ቅጽ 3 መተላለፍ ይኖርበታል::

ዓምድ 13 የምግብ፣ የመጠጥና የትንባሆ ኮድ:- በንዑስ ዓምዶች 21-25 የሚገኙት ኮዶች ከ00001 - 02098 ብቻ መሆናቸውንና በዓምድ 12 ለተመዘገበው ለፍጆታ ለዋለው የምግብ፣ የመጠጥና የትንባሆ ዝርዝር ትክክለኛውን ኮድ በዓምድ 13 መሰጠቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ከዚህም ሌላ ኮድ ያልተሰጣቸው ዕቃዎች ካጋጠሙ ከኮድ መጽሐፍ በመውሰድ ትክክለኛው ኮድ ይሰጣቸዋል:: እያንዳንዱ በጥናቱ የተሸፈነ ቤተሰብ የተጠቀመባቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች በሙሉ አስቀድሞ በማወቅ በኮድ መጽሐፍ መዘርዘርና ኮድ መስጠት ፍጹም የማይቻል ነው:: ስለሆነም በየቅጹ የሚገኙትን ዕቃዎችና አገልግሎቶች በየቦታቸው መመደብና ኮድ መስጠት ያስፈልጋል:: የህንንም ለመተግበር የሚከተለውን ዘዴ መጠቀም ያስፈልጋል::

በኮድ በጽሐፍ ውስጥ የሌለ ዕቃ/አገልግሎት ተመዝግቦ ከተገኘ ከየትኛው ቡድን ጋር እንደሚመደብ ተቆጣጣሪውን በማማከር መመደብና በቡድኑ ውስጥ ካሉት ኮዶች ከመጨረሻው ያለውን 98 መስጠት::

ማሳሰቢያ:- ይህ አሰራር በቅጽ-3 ለሚገኙ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የሚያገለግል መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል::

ዓምድ 14 የወጪ ዓይነት:- በዚህ ዓምድ ንዑስ ዓምድ 26 መታየት ያለባቸው ቁጥሮች 1 ወይም 2 ብቻ ናቸው:: ምንም ሳይሞላለት የታለፈ ካለ ተቆጣጣሪውን በማማከር በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ይሰራል:: ይህ አሠራር ለሁሉም ቅጾች ያገለግላል::

ዓምድ 15 የገንዘቡ ወይም የዕቃው ምንጭ:- በዚህ ዓምድ ንዑስ ዓምዶች 27 እና 28 ውስጥ መታየት ያለባቸው ኮዶች ከ01-16 ብቻ ናቸው:: ከዚህ ውጭ ካጋጠመ ወይም ደግሞ ኮድ ያልተሰጠው ካጋጠመ ከተቆጣጣሪው ጋር በመመካከር ውሳኔ ማግኘት ያስፈልጋል:: ይህ አሠራር ለሁሉም ቅጾች የሚያገለግል ነው::

ዓምድ 16-17 የመጠን መለኪያ ስምና ኮድ:- በዓምድ 16 ሰፍሮ የሚገኘው በዓምድ 12 የተመዘገበው የዕቃ ዓይነት የሚለካበት የመጠን መለኪያ ስም ሲሆን መታየት ያለባቸው የመጠን መለኪያ ስሞች ግራም፣ ኩቢክ ሳንቲሜትርና ቁጥር ብቻ ናቸው:: ስለዚህ ከነዚህ ውጭ የተመዘገበ የመጠን መለኪያ ስም ሲያጋጥም ለተቆጣጣሪው በማሳወቅ መፍትሔ ማግኘት ያስፈልጋል:: በዓምድ 16 የተመዘገበው የመጠን መለኪያ ስም በዓምድ 17 በንዑስ ዓምድ 29 እና 30 ውስጥ ከተሞላው ኮድ ጋር መስማማቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ለእያንዳንዱ የመጠን መለኪያ ስም የተሰጠውን ኮድ ከኮድ መጽሐፍ የመጨረሻ ገጽ ይመልከቱ:: ለምሳሌ በዓምድ 16 የተመዘገበው የመጠን መለኪያ ስም «ግራም» ቢሆን በዓምድ 17 በንዑስ ዓምዶች 29-30 ኮድ 01 ይሞላለታል ማለት ነው::

ዓምድ 18፣ 20፣ 22 እና 24 ጠቅላላ መጠን:- በነዚህ ዓምዶች ሥር ባሉ ንዑስ ዓምዶች 31-35 ፣ 41-45 ፣ 51-55 እና 61-65 የሰፈሩ ቁጥሮች በተገቢው ቦታቸው መመዝገባቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ማለትም ቁጥሮች ከቀኝ ወደ ግራ መሞላታቸውንና በአንድ ንዑስ ዓምድ ውስጥ ከአንድ በላይ ቁጥር አለመመዝገቡን ማስተዋል ያስፈልጋል:: ዋጋው ተሞልቶ መጠኑ ካልተመዘገበ ችግሩን ለተቆጣጣሪው በማሳወቅ በወቅቱ የተጠናውን የችርቻሮ ዋጋ መጠይቅ መሠረት በማድረግ መጠኑን በዋጋው ማስላት ያስፈልጋል::

ዓምድ 19 ፣ 21 ፣ 23 እና 25 ጠቅላላ ዋጋ:- በነዚህ ዓምዶች ሥር ባሉ ንዑስ ዓምዶች 36-40 ፣ 46-50 ፣ 56-60 እና 66-70 ያሉ ቁጥሮች በተገቢው ቦታ መመዝገባቸውን ያረጋግጡ የመጠን ዓምድ ተሞልቶ የዋጋው ዓምድ ባዶ ከሆነ ተቆጣጣሪውን በማሳወቅ ዋጋው ተሰልቶ እንዲሞላ ማድረግ ያስፈልጋል::

ዓምድ 26 የ1ኛ ፣ የ2ኛ ፣ የ3ኛ እና የ4ኛ ሳምንታት ኮድ ቀድሞ የተሞላ ስለሆነ አይነካም::

## ቅጽ 3ሀ እና 3ለ

## ጠቅላላ ግብይቶች ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ (ቤተሰቡ ካገኛቸው/ከገዛቸው የምግብ፣ የመጠጥና የትንባሆ ዓይነቶች በስተቀር) ከኮድ 20101-ኮድ 95098

ይህ ቅጽ የሚያገለግለው የተመረጠው ቤተሰብ ጥናቱ በሚመለከተው ሳምንትና ጉብኝት ወቅት ውስጥ:-

I. ለቤተሰቡ ጥቅም የዋሉ/የሚውሉ የልብስ፣ የጫማና በራስ ላይ የሚጠለቅ ጠቅላላ የመጠንና ዋጋ መረጃዎች ሰፍረዋል፡፡ ለነዚህ ዕቃዎችና አገልግሎቶች መታየት ያለባቸው ኮዶች 20101-20598 ብቻ ናቸው፡፡ ከነዚህ ውጭ ካጋጠመ ኮድ መጽሐፍ ገጽ 11-16 መሠረት መስተካከል ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም በኮድ መጽሐፍ ውስጥ የሌለ ዕቃ ከሆነ ለቅጽ 2 በተሰጠው መመሪያ መሠረት ይሰራል፡፡

II. የተመረጠው ቤተሰብ የከፈለውን የቤት ኪራይ፣ ለቤት ጥገናና እንክብካቤ፣ ለተለያዩ የኢነርጂ ዓይነቶችና የውኃ መጠንና ዋጋ የሚመዘገብበት ነው፡፡ ለእነዚህ ዕቃዎችና አገልግሎቶች መታየት ያለባቸው ኮዶች 30101-30498 ብቻ ናቸው፡፡ ከነዚህ ውጭ ካጋጠመ ኮድ መጽሐፍ ገጽ 17-19 መሠረት መስተካከል አለበት፡፡ እንዲሁም በኮድ መጽሐፍ ውስጥ የሌለ ዕቃ ከሆነ ከላይ በተሰጠው መመሪያ መሠረት ይሰራል፡፡

III. የተመረጠው ቤተሰብ የከፈለበትን/ያልከፈለበትን የቤት ቁሳቁስ፣ ለቤት ሠራተኛና እንዲሁም ለሌሎች ያገልግሎት ክፍያዎች ጠቅላላ መጠንና ጠቅላላ ዋጋ መመዝገቢያ ነው፡፡ ለነዚህ ዕቃዎችና አገልግሎቶች መታየት ያለባቸው ኮዶች 40101-41398 ብቻ ናቸው፡፡ ከነዚህ ውጭ ካጋጠመ ኮድ መጽሐፍ ገጽ 20-26 መሠረት መስተካከል አለበት፡፡ እንዲሁም በኮድ መጽሐፍ ውስጥ የሌለ ዕቃ ከሆነ ከላይ በተሰጠው መመሪያ መሠረት ይሰራል፡፡

IV. የተመረጠው ቤተሰብ ለጤና፣ ለትምህርት፣ ለመጓጓዣና መገናኛ እንዲሁም ለመዝናኛ ያወጣቸውን ወጪዎች መመዝገቢያ ነው፡፡ ለነዚህ ዕቃዎችና አገልግሎቶች መታየት ያለባቸው ኮዶች 50101-70498 ብቻ ናቸው፡፡ ከነዚህ ውጭ ካጋጠመ ኮድ መጽሐፍ ገጽ 27-33 መሠረት መስተካከል አለበት እንዲሁም በኮድ መጽሐፍ ውስጥ የሌለ ዕቃ ከሆነ ከላይ በተሰጠው መመሪያ መሠረት ይሰራል፡፡

V. የተመረጠው ቤተሰብ ለግል ንጽህና፣ ለግል ቋሚ ዕቃዎች ለጌጣጌጥና ለሌሎች የቤተሰብ ወጪዎች (ከላይ ከተዘረዘሩት ወጪዎች ካወጣው ሌላ) የተመዘገቡበት ነው፡፡ ለነዚህ ዕቃዎችና አገልግሎቶች መታየት ያለባቸው ኮዶች 80101-90304 ብቻ ናቸው፡፡ ከነዚህ ውጭ ካጋጠመ ኮድ መጽሐፍ ገጽ 34-36 መሠረት መስተካከል አለበት፡፡ እንዲሁም ከኮድ መጽሐፍ ውስጥ የሌለ ዕቃ ከሆነ ከላይ በተሰጠው መመሪያ መሠረት ይሰራል፡፡

VI. የተመረጠው ቤተሰብ ለቤተሰቡ ፍጆታ ሳይሆን ሌሎች ጉዳዮች ያወጣቸው ወጪዎች/ለምሳሌ:- ለዕቁብ፣ ለዕድር፣ ለተለያዩ መዋጮዎች፣ ለቤተሰቡ ድርጅት ...ወዘተ/መመዝገቢያ ነው:: እነዚህ ወጪዎችና ኮድ ዝርዝራቸው በኮድ መጽሐፍ ገጽ 37 ላይ የሚገኝ ሲሆን ከኮድ 95001-ኮድ 95098 ያሉትን ያጠቃልላል::

VII. ቤተሰቡ በጥሬ ገንዘብ ብቻ ያገኘው የገቢ መጠን የሚመዘገብበት ነው:: መታየት ያለበት ኮድ 19190 ብቻ ነው:: የቤተሰብ ገቢ በገንዘብና በዕቃ መልክ የሚገኝ ቢሆንም ይህ ኮድ መሰጠት ያለበት ግን በጥሬ ገንዘብ ለተገኘ ገቢ ብቻ መሆን አለበት:: ለሌሎች በዓይነት ለተገኙ ገቢዎች እንደ ምድባቸው ተስማሚውን ኮድ መስጠት ያስፈልጋል::

በቅጹ ራስጌ የአካባቢው መለያ ስሞችና የመሳሰሉት በትክክል መሞላታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

<u>ዓምድ 12</u> <u>የገቢ፣ ወጪና ፍጆታ ዕቃዎች ዝርዝር</u>:- በዚህ ቅጽ መመዝገብ ካለባቸው ዕቃዎች/አገልግሎቶች ውጭ ማለትም ከላይ ከተራ ቁጥር I - VII ካሉት ውጭ ካጋጠመ ሁኔታውን በደንብ አጣርቶ ከተረጋገጠ በኋላ ወደ ቅጽ 2ሀ ና 2ለ ማስተላለፍ ያስፈልጋል:: ለምሳሌ ቅጽ 3ሀ ና 3ለ ውስጥ የእህል ዓይነቶች ተዘርዝረው ብናገኝ እነዚህን እህሎች ቤተሰቡ ለቤተሰቡ የምግብ ፍጆታ ያዋለው ከሆነ ወደ ቅጽ 2ሀ ና 2ለ ይተላለፋሉ:: ነገር ግን ቤተሰቡ እህሉን ገዝቶ ለማስቀመጥ ከሆነ ከቅጽ 3ሀ ና 3ለ ላይ ይሰረዛል:: ቤተሰቡ ለቤተሰቡ ድርጅት ለማዋል እህሉን ገዝቶ ቢሸጥ ጠላ ጠምቆበት ቢሸጠው እና ለመሳሰሉት ተግባራት ሊያውለው ከሆነ እዚሁ ቅጽ ላይ እንዳለ ተስማሚው ኮድ ይሰጠዋል::

<u>ዓምድ 13</u> <u>የዕቃው ዓይነት ኮድ</u>:- በዓምድ 12 ለተመዘገቡት በዓምድ 13 የተሰጣቸው ኮድ ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ኮድ ያልተሰጠው ዕቃ/አገልግሎት ከተገኘ ትክክለኛውን ኮድ መስጠት ያስፈልጋል::

<u>ዓምድ 14-15</u> የወጪ/ገቢ ዓይነትና ምንጭ ለቅጽ 2 የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ

<u>ዓምድ 16-17</u> <u>የመጠን መለኪያ/ስምና ኮድ</u>:- ለቅጽ 2 የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ

<u>ማስታወሻ</u>:- የሚከተሉት የዕቃ ኮዶች ማለትም የማስፈጫ ዋጋ ኮድ 41301 ፣ 41302 እና 41303 ፣ የመጋገሪያ ዋጋ ኮድ 41304 እንዲሁም ለአራጅ የተከፈለ ኮድ 41305 የመጠን መለኪያ ስምና ኮድ አያስፈልጋቸውም::

<u>ዓምድ 18 ፣ 20 ፣ 22 ፣ 24</u>:- ጠቅላላ መጠን በነዚህ ዓምዶች ሥር ባሉ ንዑስ ዓምዶች 31-37 ፣ 43-49 ፣ 55-61 እና 67-73 የሰፈሩት ቁጥሮች በተገቢው በታቸው መመዝገባቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ማለትም ቁጥሮች ከቀኝ ወደ ግራ መሞላታቸውንና በአንድ ንዑስ ዓምድ ውስጥ ከአንድ በላይ ቁጥር አለመመዝገቡን

ማስተዋል ያስፈልጋል:: ዋጋው ተሞልቶ መጠኑ ካልተመዘገበ፣ ችግሩን ለተቆጣጣሪው በማሳወቅ በወቅቱ የተጠናውን የችርቻሮ ዋጋ መጠይቅ መሠረት በማድረግ መጠኑን በዋጋው ማስላት ያስፈልጋል:: ለመጠን መጻፊያ የተሰጠው ቦታ በቂ ባለመሆኑ መጠኑ ከቅጹ ውጭ ከተጻፈ መጠኑን ለሁለት በማካፈል ሁለት ጊዜ በሁለት መስመር መጻፍ ያስፈልጋል::

ዓምድ 19 ፣ 21 ፣ 23 ፣25:- ጠቅላላ ዋጋ በነዚህ ዓምዶች ሥር ባሉ ንዑስ ዓምዶች 38-42 ፣ 50-54 ፣ 62-66 ፣ 74-78 ያሉ ቁጥሮች በተገቢው ቦታ መመዝገባቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: የመጠን ዓምድ ተሞልቶ የዋጋው ዓምድ ባዶ ከሆነ ለተቆጣጣሪው በማሳወቅ ዋጋው ተሰልቶ እንዲሞላ ማድረግ ያስፈልጋል:: ለዋጋ መጻፊያ የተሰጠው ቦታ የማይበቃ ሆኖ ከቅጹ ውጭ ከተጻፈ ዋጋውን በሁለት በማካፈል ሁለት ጊዜ መጻፍ ያስፈልጋል::

ዓምድ 26 የ1ኛ ፣ የ2ኛ ፣ የ3ኛ እና የ4ኛ ሳምንታት ከድ ቀድሞ የተሞላ ስለሆነ አይነካም::

## ቅጽ - 4

ባለፈው ስድስት ወራት ቤተሰቡ ወጪ ያወጣባቸው ዕቃዎች/አገልግሎቶች ዋጋ መመዝገቢያ:- በቅጹ ራስጌ የአካባቢው መለያ ስሞችና የመሳሰሉት በትክክል መሞላታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ዓምድ 12-13 አስቀድሞ የተሞላ ስለሆነ አይነካም::

ዓምድ 14 ያለፉት 6 ወራት ወጪ/ገቢ ጠቅላላ ዋጋ:- ቤተሰቡ በዓምድ 12 ለተዘረዘሩት የዕቃ ዓይነቶች ባለፉት 6 ወራት የከፈለው ዋጋ በትክክል መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: እንዲሁም በቅጽ 3 ላይ የተመዘገቡ በቅጽ 4 ዓምድ 12 ላይ የተዘረዘሩት ዕቃዎች ካሉ ጠቅላላ የወሩ ዋጋቸው ወደ ቅጽ 4 መተላለፉን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

## ቅጽ - 5

ቤተሰቡ ባለፉት 6 ወራት በጥሬ ገንዘብ ያገኘው የገቢ መጠንና ቤተሰቡ የሚኖርበት ቤት ይዞታ ሁኔታ:- በቅጹ ራስጌ የአካባቢው መለያ ስሞችና የመሳሰሉት በትክክል መሞላታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ዓምድ 12-13 አስቀድሞ የተሞላ ስለሆነ አይነካም::

ዓምድ 14:- ቤተሰቡ ባለፉት 6 ወራት ውስጥ ያገኘው ገቢ የሚመዘገብበት ነው:: በዚህ ዓምድ ውስጥ ቁጥሮች በትክክል መሞላታቸውን ማስተዋል ያስፈልጋል:: እንዲሁም

በቅጽ 3 ላይ በጥሬ ገንዘብ የተገኘው ገቢ ወደ እዚህኛው ቅጽ መተላለፉን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ዓምድ 15:- ቤተሰቡ የሚኖርበትን መኖሪያ ቤት በምን መልኩ እንደያዘው ተጠይቆ የሚሞላበት ቅጽ ነው:: በዓምዱ ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛው ኮድ በንዑስ ዓምድ 30-31 ውስጥ በትክክል መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: እንዲሁም በዚህኛው ዓምድ የተሰጠው መልስና በቅጽ 3 ላይ ስለ ቤት (ማለትም የቤት ኪራይ የኪራይ ግምት እና በነፃ የሚኖርበት ቤት የኪራይ ግምት) ከተሞላው መረጃ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::